ከአዳኝ ወይም ከከብት ጠባቂ ውሻ ውጪ የሆነ ውሻን ያሳደገ ሰው በየቀኑ ከስራው ሁለት ቂራጦች ይቀነሱበታል።

ከኢብኑ ዑመር (ረዲየሏሁ ዐንሁማ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና
ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ አሉ: «"ከአዳኝ ወይም ከከብት ጠባቂ ውሻ ውጪ የሆነ ውሻን ያሳደገ ሰው በየቀኑ ከስራው ሁለት ቂራጦች ይቀነሱበታል።" ሳሊም እንዲህ አለ: አቡ ሁረይራም የእርሻ ባለቤት ነበርና "ወይም የእርሻ ጠባቂ ውሻ ካልሆነ" ይል ነበር።» [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ለአደን ወይም ለከብቶችና አዝርዕት ጥበቃ ፈልጎ ካልሆነ በቀር ውሻን ከማሳደግ ከለከሉ። ከነዚህ ውጪ ለሆነ አላማ ያሳደገ ሰውም በየቀኑ ከስራው ሁለት ቂራጥ ምንዳ ይቀነስበታል። ቂራጥ ሲባል የተፈለገው መጠንን የሚያውቀውም አላህ ብቻ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/2994